# መንገዳችን!

እሁድ ዕለት ግንቦት 29 ቀን 2002 (June 6, 2010)፣ ግርማሞገስ girmamoges@yahoo.com

በምርጫ 2002 ኢህአዴግ/ህውሃት በኢትዮጵያ የፉክክር ፖለቲካን ቀውስ ከቶታል። ለኢትዮጵያ ምርጫዎች ቀርበውላታል። ወደ ቀድሞው አንድ የፖለቲካ ፓርቲ ስርዓት መመለስ ወይንም አለመመለስ። ህጋዊ የፖለቲካ ፓርቲዎች ወደ ዘላለማዊ መረሳት ሊያመሩ ወይንም ወደ መደብለ ፖለቲካ ፓርቲ ስርዕት ሊመሩን። ኢህአዴግ/ህውሃት በ1983 ዓ. ም. በደርግ ላይ ያገኘውን ወታደራዊ ድል፣ በ2002 ዓ. ም. ምርጫ ደግሞ በዴሞክራሲ ላይ ሊደግም ወይንም ፍጻሜውን ሊጀምር። እነዚህ አማራጮች ተደቅነውባታል ኢትዮጵያ። ይኼን ቀውስ ለመቆጣጠር የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ፓርቲዎች፣ በኢትዮጵያ ውስጥ እና ከኢትዮጵያ ውጭ ያሉ ኢትዮጵያውያን የሚወስዱዋቸው እርምጃዎች የኢትዮጵያን አቅጣጫ ይወስናሉ።

በኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ሂደት ላይ የደረሰውን ቀውስ ለመቆጣጠር ወይንም ለማስወገድ ምን እናድርግ? የሚቀጥለው ትግላችን ምንድን ነው? የሚሉ ጥያቄዎች ተነስተዋል። የመፍትሄ አሳቦች እና ትንታኔዎች ከየአቅጣጫው እየዘነቡ ነው። የቀረቡትን የመፍትሄ አሳቦች ከሶስት ጎራ ልንፈርጃቸው እንችላለን። እነሱም (1ኛ) ኃይል በመጠቀም (የትጥቅ ትግል) ኢህአዴግ/ህውሃትን ከስልጣን መፈንቀል፣ (2ኛ) እጅ አጣምሮ በመቀመጥ የኢህአዴግን/የህውሃትን በጎ ፈቃደኛነት መጠበቅ እና (3ኛ) ሰላማዊ እና ህጋዊ ትግል ማድረጉን መቀጠል የሚሉ አማራጭ መንገዶች ናቸው። በዚህ ጽሑፍ እነዚህ አማራጭ መንገዶች በአጭር በአጭሩ ይመረመራሉ። አማራጭ መንገዳችን ተለይቶ ይወጣል። ለቀውሱ ምክንያቶች ከሆኑት ውስጥ ጥቂቶቹ ይቀርባሉ። ምን ቢደረግ ይበጃል? ለሚለውም ግርድፍ የመወያያ መፍትሄ አስቦች ይሰነዘራሉ።

### (1ኛ) ኢህአዴግን/ህውሃትን በኃይል የማውረድ (የትጥቅ ትግል) አማራጭ

ይኼን አማራጭ የሚያራምዱ ወገኖች ኢህአዴግን/ህውሃትን በጦር ኃይል መፈንቀል ያስፈልጋል ይላሉል። እነዚህ ወገኖች ጫካ መግባትን የሚመርጡት ወደው አይደለም። ጫካ በችግር እንጂ በድሎት መኖሪያ ቦታ አይደለም። ገዢው ፓርቲ የፖለቲካ ምህዳሩን ሲያጥብ እና በሰላማዊ መንገድ መታገልን የማይቻል ሲያደርግባቸው ጫካ መግባትን ይመርጣሉ። በምርጫ 2002 ኢህአዴግ/ህውሃት በመላ ኢትዮጵያ ከምርጫው ሂደት ጀምሮ እስከ ፍጻሜው ድረስ በመራጩ ህዝብ፣ በተቃዋሚ ፓርቲዎች፣ በእጩዎቻቸው እና ታዛቢዎቻቸው ላይ የፈጸማቸው ግፎች፣ አይን ያወጣ የህዝብ ድምጽ ዘረፋ እና የምርጫ ቦርድ ትብብር ብዙዎችን ሰላማዊ ትግል

ቢያንገፈግፋቸው ሊገርመን አይገባም። ይሁን እንጂ ምን ማድረግ እንዳለብን እና እንዴት እንደምንታገል አጀንዳችንን የሚቀይስልን አምባገንኖች መሆን የለባቸውም የሚል እምነት አለኝ። ኢትዮጵያ የምትገኝበትን ሁኔታ እና የመንግስት ሽግግር ታሪካችንን ከግንዛቤ ስናስገባ ይኼ አማራጭ ተመራጭ መንገዳችን አይመስለኝም። በጥቂቱ ላብራራ።

(1) ይህ አማራጭ ለኢትዮጵያ አዲስ አይደለም። ከአክሱም ስልጣኔያችን ቀደም ሲል ጀምሮ ኢህአዴግ ስልጣን ላይ እስከወጣበት ድረስ በነበሩት በሺዎች የሚቆጠሩ አመታት ውስጥ ይኼ አማራጭ የመንግስት ለውጥ መፈጸሚያ ባህላችን ሆኖ ቆይቷል። የቀድሞ አባቶቻችን የነበራቸው የስልጣኔ እና የእውቀት ደረጃ ውሱን ስለነበር ይኼን ዘዴ ተጠቅመውበታል። ለዛሬ አዕምሮዋችን ግን ይኸን የትናንት ኋላቀር ያልተገራ ዘዴ መውረስ እና መቀጠል ያስቸግረዋል። የመንግስት ሽግግር ባህላችን መገራት አለበት። ለሙብረር ሁለት ክንፍ እንደሚያስፈልገው ሁሉ ለጦርነትም ሁለት ተዋጊ ኃይሎች መኖር አለባቸው። እስከ ምርጫ 2002 ድረስ ተቃዋሚው በሰላማዊ መንገድ እታገላለሁ ማለቱ ብቻ የመንግስት ሽግግር ባህላችን በ50 ከመቶ ያህል እንዲገራ አድርጎታል። የቀረውን 50 ከመቶ ለመግራት ደግሞ የሚያስፈልገው አዕምሮዋችንን እና አቅማችንን አንድ አድርገን ኢህአዴግ/ህውሃት መታገል በማችልበት ደካማ ጎኑ መግጠም ነው። ለኢህአዴግ/ህውሃት ጠበንጃ መጠቀም ጠንካራ ጎኑ ነው። ህግ አክብሮ ሰላማዊ ትግል ማድረግ ግን ደካማ ጎኑ ነው። ስለዚህ ዛሬ ያልተገራውን ቀሪውን 50 ከመቶ የመንግስት ሽግግር ባህላችንን ለመግራት እና ህዝባችንን የመንግስት ስልጣን ባለቤት ለማድረግ ኢህአዴግ/ህውሃትን በደካማ ጎኑ መግጠም ይመረጣል።

(2) የትጥቅ ትግል ፖለቲካውን ወደፊት የሚያራምደው እና ቡድኑን ከስልጣን የሚያስቀምጠው እንደ ሰላም ትግል በእውቀት፣ በችሎታ፣ በብቃት፣ በፉክክር እና በህዝብ ምርጫ ሳይሆን በእርስ በርስ መገዳደል ነው። በመገዳደል አብላጫ ጦር ያለው እና በጦር ሜዳ ድል የቀናውን ቡድን ስልጣን ላይ ይወጣል። እርስ በርስ መገዳደል ሊበቃን ይገባል።

(3) በታሪካችን በጦርነት (በትጥቅ ትግል) የተመሰረቱትን መንግስታት በሙሉ መላው ህዝባችን ፈቅዶ ተቀብሎዋቸው አያውቅም። ዛሬም የኢህአዴግ/ህውሃት መንግስት ችግር ይሔው ነው። ህውሃት በቀረው ኢትዮጵያ ህጋዊነትን ለማግኘት ኢህአዴግ በሚባል ሽማ ቢጠቀለልም አልተሳካለትም። ኢህአዴግ መጀመሪያ የምርኮኞች ከዚያ የደሞዝተኞች ህብረት እንጂ ከህውሃት በስተቀር ሌሎቹ አባል ድርጅቶች ወክልንህ የሚሉትን የህዝብ ክፍል ቀደም ሲል አደራጅተው እና አታግለው ለድል ያበቁ እንዳልሆኑ ህዝብ ያውቀዋል። በዚህ ዘዴ ስልጣን ላይ የሚወጣ

ቡድን ከህዝቡ የእኛ መንግስት ነው የሚል ተቀባይነት ትናትም ሆነ ዛሬ አላገኘም አያገኝም። ስለዚህ ህዝቡ የመረጠው መንግስት ስልጣን ላይ የሚወጣበትን መንገድ ብንመረጥ ይሻላል።

(4) በዚህ አማራጭ ስልጣን የጨበጡ ገዢዎችን ማንነት፣ ምንነት፣ ችሎታ፣ ብቃት፣ የአዕምሮ ዝንባሌ እና ጤንነት ህዝቡ የሚያውቀው እንደ ሰላማዊ ትግል ስልጣን ከመጨበጣቸው በፊት ሳይሆን ስልጣን ከጨበጡ እና ጠበንጃቸውን በጭንቅላቱ ላይ ከደቀኑ በኋላ ነው። ይህ አማራጭ የአዕምሮ ዝንባሌያቸው ወይንም ጉድለት ለአገር መሪነት ብቁ የማያደርጋቸው ሰዎች ሳይቀሩ ስልጣን ላይ እንዲወጡ ሊያደርግ ይችላል። እንደዚህ አይነት ሰዎች ደግሞ እንኳን ለአገር ሉዓላዊነት፣ ለህዝብ አንድነት እና ለአገር እድገት አንድ ቤተሰብ ለማስተዳደርም አደገኛ ሊሆኑ ይችላሉ። ስለዚህ ይኼን አማራጭ መምረጥ የለብንም።

(5) በዚህ አይነት መንገድ ስልጣን ላይ የሚወጡ መሪዎች አገር መምራት የሚጠይቀውን ዝርዝር እውቀት እና ልምድ የሚያካብቱት ስልጣን ላይ ከወጡ በኋላ ስለሆነ አገርን፣ ህዝብን እና የአገር ሃብትን መለማመጃ ያደርጋሉ። አዋቂዎች ከአገር የሚሰደዱበት ሁኔታም ሊፈጠር ይችላል። ብዙ ሃብት ይባክናል። ስለዚህ ይህ አማራጭ መጥፎ ምርጫ ነው።

(6) ይህ የትግል ዜዴ የፖለቲካ ድልን (የመንግስት ስልጣን መጨበጥን) የሚቀዳጀው ደም በማፍሰስ፣ በመግደል እና የአገር ሃብት በማውደም ነው። የፖለቲካ ባህሉ ደም የተጸናወተው ነው። ስብዕናውም ዝቅተኛ ነው። ድል አድራጊው ቡድን ለገዢነት ወደ ከተሞች ሲገባም ይህን ደም የጠገበ የፖለቲካ ባህል እና ዝቅተኛ ስብዕና ተሸክሞ ከሰላማዊው ህዝብ ጋር ተቀላቅሎ በህዝብ ውስጥ ያሰራጨዋል። እንዲሁም በከተሞች ውስጥ ብረት የሚያነሱ ድርጅቶችም ሳይቀሩ ተመሳሳይ የባህል እና የስብዕና ውድቀት ውስጥ ይገባሉ። ደም ማፍሰስን እንደ ትግል ዘዴ የሚጠቀም የፖለቲካ ኃይል ወደደም አልወደደ፣ አወቀም አላወቀ፣ መረጠም አልመረጠ የስብዕና ቀውስ ይደርስበታል። በህውሃት፣ በሻቢያ እና ሌሎች የትጥቅ ትግል ድርጅቶች ውስጥ የተፈጸሙ አንዳንድ ማብራሪያ የሚሆኑ የታሪክ መረጃዎችን ማቅረብ ይቻላል። ይህን ጽሑፍ እያዘጋጀሁ ሳለ ጊዜ ሳገኝ ምስክርነት (በባለስልጣናቱ አንደበት) የሚለውን በሻንበል ተስፋዬ እርስቴ መኮንን የተጻፈውን መጽሐፍ ሳነብ በአዲስ አበባ የመንግስት ባለስልጣናት ቡና ቤት አምሽተው ሰክረው ሲመለሱ በእስር ቤቶች የነበሩ የኢሕአፓ አባላትን ለሊት ከታሰሩበት እያወጡዋቸው ተኩስ መለማመጃ ያደርጓቸው እንደነበር፣ በብዛት እያወጡም ይገድሉዋቸው እንደነበር እና መጨረሻ በደህንነት ምኒስትሩ መመሪያ ባለስልጣናቱ ሰክረው መግደል እንዲያቆሙ መደረጉን በገጽ 177-178 ላይ ያመለከታል። ይህ የህብረተሰብ ሰብዓዊነት ቀውስ ነው። እርግጥ ኢትዮጵያ ከዚህ የከፉትን እነ ቀይ ሽብርንም አስተናግዳለች። በገጠርም ደርግ

የነጻ አውጪዎች ተባባሪዊች ናቸው ብሎ የጠረጠራቸውን፣ ነፃ አውጪዎችም የደርግ ተባባሪ ያሉዋቸውን ገበሬዎች፣ ከብት አርቢዎች እና ባላባቶች ገድለዋል። ቤታቸውን አቃጥለዋል። ሃብታቸውን ዘርፈዋል። በከተማም በገጠርም ተመሳሳይ ሁኔታ ተመልሶ ሊመጣ ስለሚችል ይህ አማራጭ ተራማጅ አማራጭ አይደለም።

(7) የትጥቅ ትግል ከተመረጠ ያልተቋረጠ የጦር መሳሪያ፣ የገንዘብ እርዳታ፣ የህክምና እና ሌሎች አስፈላጊ ነገሮችን የሚቀልቡ ምንጮች ያስፈልጋሉ። መሸሸጊያ፣ ጦር ማሰልጠኛ እና ሌሎች ከጦርነት ጋር ተዛማጅ የሆኑ ጉዳዮችም ሊያስፈልጉ ይችላሉ። በጦርነት መንግስት ለመፈንቀል የተሰማሩ ኃይሎች እነዚህን ነገሮች ለማሟላት ሲሉ በታሪካችን ከኢትዮጵያ ጠላቶች ጋር እስከ መመሳጠር የደረሱባቸው ጊዚያት ብዙ ናቸው። በዚህ ላይ እርዳታ የሚለግሱዋቸው አገሮች በበጎ አድራጎት ስራ ላይ የተሰማሩ አይደሉም። እርዳታ የሚለግሱት የግል የፖለቲካ ጠቀሜታቸውን ለማራመድ ነው። ኢትዮጵያን ደካማ አገር ማድረግ ከሆነ የፖለቲካ ጠቀሜታቸው እሱን ለእነዚህ ኃይሎች የጦር መሳሪያ፣ የገንዘብ እና ሌሎች እርዳታዎች በማድረግ የኢትዮጵያን አንድነት ለማናጋት ይሞክራሉ። ከታሪካችን ብዙ ምሳሌዎች መጥቀስ ይቻላል። ያገር ተወላጆች በስልጣን ላይ ያለውን ባላንጣቸውን በጦር ለመፈንቀል ሲሉ ጥንት በመካከለኛው ክፍለ ዘመን ኦቶማን ቱርክ ምጽዋን ይዛ በነበረበት ጊዜ ከቱርክ፣ ከዚያ በቴዎድሮስ ዘመነ መንግስት ከፈረንሳይ፣ ከግብጽ፣ ከቱርክ እና ከእንግሊዝ፣ በዮሐንስ ዘመነ መንግስት ከግብጽ እና ከኢጣሊያ ጋር ትብብሮች ተደርገዋል። በምኒልክ ዘመነ መንግስት ረገብ ቢልም ይኼ ከኢትዮጵያ ባላንጣ መንግስታት ጋር መተባበር በኃይለ ስላሴ እና በደርግ ዘመን አገርሽቶበት በትጥቅ በተሰማሩ የተለያዩ ድርጅቶች መሪዎች ተፈጽሟል። ዝርዝር ውስጥ አልገባም። አሁንም የጦርነትን መንገድ የመረጡ የኢህአዴግ/ህውሃት መንግስት ባላንጣዎች ኢትዮጵያን ለመበተን ያልፈነቀለው ድንጋይ ካልነበረው እና አሁንም ካልተኛው ከኢሳያስ አፈወርቂ ጋር ስለመወዳጀታቸው በሰፊው ተዘግቧል። በአባይ ወንዝ የተነሳ በኢትዮጵያ የውስጥ ጉዳይ በመግባት ኢትዮጵያን ለማዳከም ሁልጊዜ ከማይተኙት አገሮች ውስጥ ዋንኛዋ ግብጽ ነች። የሆነው ሆኖ በትጥቅ ትግል ወይንም በጦርነት መንግስት የማስወገድን አማራጭ የተቀበሉ ኃይሎች ወደዱም አልወደዱ በኢ-አገር ወዳድ (Unpatriotic) ተግባሮች እንዲሰማሩ ይገደዳሉ። ዛሬም እንደትናቱ ይኼን አሳፋሪ ባህል መቀጠል የለብንም። ኢትዮጵያ ከማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ወይንም ቡድን ፖለቲካዊ ምኞት የበላይ መሆኗ መዘንጋት የለበትም። ስለዚህ በጦርነት መንግስት የመፈንቀሉ አማራጭ በዚህ ተጨማሪ ምክንያት የተነሳ ውድቅ መደረግ አለበት።

(8) በጦርነት መንግስት የመለወጥ ባህላችን በኢትዮጵያ ላይ ከፍተኛ ኪሳራ (በሃብትም በነፃነትም) ሲያደርስ ቆይቷል። እሩቅ ሳንሄድ በደርግ ዘመን በተደረገው የትጥቅ ትግል (የእርስ በርስ ጦርነት) ኢትዮጵያ ያገኘችውን ጥቅም ከደረሰባት ጉዳት ጋር በአጭሩ እናነጻጽር።

(ሀ) 90 ከመቶ በላይ በሆነ ድምጽ ተመረጥኩ ሲለን የነበረው አምባገነኑ ደርግ ቢሄድም በእግሩ 90 ከመቶ በላይ በሆነ ድምጽ አሸነፍኩ የሚለን ኢህአዴግ የሚባል አዲስ አምባገነን ተተካ። መንግስቱ ኃይለማሪያም በትጥቅ ትግል ቢፈነቀልም የመንግስቱ የፖለቲካ ታናሽ ወንድም መለስ ዜናዊ በእግሩ ተተካ። ስለሆነም የትጥቅ ትግሉ ከአምባገነን ወደ አምባገነን ወሰደን እንጂ ህዝብን የስልጣን ባለቤት በማድረግ ረገድ ምንም ጥቅም አልተገኘም። ምንም የወደፊት እርምጃ አልተደረገም።

(ለ) በደርግ ዘመን የተደረገው የትጥቅ ትግል ኢትዮጵያ ኤርትራን እንድታጣ አደረገ። ኢትዮጵያ ኤርትራን ስታጣ የአንድ ክፍለ አገር የሰው ሃብት፣ የክፍለ አገሪቱ ምድር በውስጡ እና በውጭው ያለውን ሃብት እንዲሁም የባህር በር አጣች። ኢትዮጵያ ለወደብ ግልጋሎት በአመት በቢሊዮን ብር የሚቆጠር የአሜሪካ ብር እንድትከፍል ተደረገች። እስከዚህ ድረስ እንዳየነው የትጥቅ ትግሉ ለኢትዮጵያ ጉዳት እንጂ ጥቅም አላመጣም።

(ሐ) የትጥቅ ትግሉ ኢሳያስን የመሰለ አምባገነን በኤርትራ አንግሶ የኤርትራን ህዝብ በትግሪኛ ቋንቋ ተናጋሪ አምባገነኖች እንዲጨቆን አደረገ። ኢሳያስ በመላ የአፍሪካ ቀንድን የፖለቲካ መረጋጋት እንዲጥፋ አደረገ። ጥቅም የለም ኪሳራ (ጉዳት) እንጂ።

(መ) ኢትዮጵያ የኤርትራን ህዝብ (ሃብት)፣ የክፍለ አገሩ ምድር በውስጡ ያቀፈውን እና በውጭው የያዘውን ሃብት እና የባህር በር ሃብት በማጣቷ ላይ በተጨማሪ በትጥቅ ትግሉ የተነሳ ያለቀውን ህዝብ፣ የወደመውን የጦር መሳሪያ እና ተዋጊ፣ የወደመውን የአገር ሃብት (መንገዶች፣ ህንጻዎች ወ.ዘ.ተ.)፣ በጦርነት ላይ የተሰማሩት ኢትዮጵያዊ ድርጅቶች (ህውሃት፣ ደርግ፣ ሌሎችም) ለጦር መሳሪያ ያፈሰሱት ገንዘብ፣ በጦርነት ምክንያት የቆመው የአገር እድገት እንዲሁም በትጥቅ ትግሉ የተነሳ በወሎጋ፣ በከፋ፣ በወሎ፣ በትግራይ የደረሰው ድርቅ ያስከተለው ጉዳት በሙሉ በብር ($) ብንተምነው በኢትዮጵያ ላይ የደረሰው ኪሳራ ጭንቅላታችን በመብረቅ የተመታ ይመስለናል። ይህ ብቻ አይደለም።

(ሠ) የባህር በር ማጣቱ የባህር ላይ ንግድ እና የጦር መሳሪያ እንደልብ ከውጭ የማስገባት ነጻነታችንን ነጥቆን የሌሎች አገሮች ጥገኛ አድርጎናል። ጥገኛ መሆን የነፃነትን ደረጃ ዝቅ ያደርጋል። በመንግስታት መካከል ያለው ግንኙነት የጥቅም ግንኙነት ነውና አንድ ቀን

ያውም በመጥፎ ቀን ዛሬ የወደብ ግልጋሎት የሚሰጡን አገሮች ከውጭ ጠላቶቻችን ጋር መተባበር የበለጠ ጥቅም ካስገኘላቸው ወደቦቻቸውን ሊዘጉብን እንደሚችሉ መጠራጠር የለብንም። ለምሳሌ በሁለተኛው የአለም ጦርነት ዋዜማ ኢጣሊያ ኢትዮጵያን በመውረር ላይ ሳለች ፈረንሳይ ከኢትዮጵያ የጅቡቲ ወደብ መጠቀም ከምታገኘው ጥቅም በአውሮፓ ኢጣሊያ ከሂትለር ጋር እንዳይተባበር ማድረግ ስለበለጠባት ፈረንሳይ ለኢጣሊያ ማግባቢያ ስትል በኢትዮጵያ ላይ የጅቡቲን ባህር በር ዘግታ ኢጣሊያ እንድትጠቀምበት ማድረጓ የሚታወስ ታሪካችን ነው። በዚያን ጊዜ በሰማይ የሚበር አይሮፕላን የሌላት ኢትዮጵያ የጦር መሳሪያ ማስገቢያ ቀዳዳ አጣች። በዚህ አይነት ለጅም ጊዜ ኢትዮጵያን ትደግፍ የነበረች ፈረንሳይ ኢትዮጵያን ለኢጣሊያ ሰጠች። ትንሽ ቀየርየር ቢልም ከሞላ ጎደል ተመሳሳይ ሁኔታ ወደፊት መልሶ አይደገምም ማለት አይቻልም። ስለሆነም የትጥቅ ትግል ያደረሰብን ኪሳራ የነፃነታችንንም ጥንካሬ አዳከሟል። ኪሳራ ብቻ!

(9) እርግጥ ነው ዛሬ አለም አቀፋዊው ሁኔታው ለትጥቅ ትግል የሚውል የጦር መሳሪያ እንደልብ ከቦታ ወደ ቦታ ማዘዋወር እንዳይቻል አድርጓል። ስለሆነም ከእነ ኢሳያስ ወይንም ከግብጽ እና ከሱዳን መንግስት ወይንም ከአልሸባብ ነፃ የሆነ በአጭር ጊዜ ውጤት የሚያመጣ ህብረ ብሔራዊ የትጥቅ ትግል ማድረግ አዳጋች ነው የሚል ሙግትም ማቅረብ ይቻላል።

ሲደመደም፥ በኢትዮጵያ በጦር ኃይል (እርስ በርስ መገዳደል) መንግስት መቀየር አሮጌ አስተሳሰብ ነው። ኢትዮጵያ ላይ መገመት የሚያስቸግር ውድቀት አድርሷል። ዛሬ ያለው አለም አቀፋዊ ሁኔታ ለሰላም ትግል እና ለፉክክር ፖለቲካ ምቹ ነው። ይህን እድል ለመጠቀም ግን በሰላም ትግል ፍልስፍና እና ዘዴዎች የበሰሉ መሪዎች እና የሰላም ትግል አርበኛ ያስፈልጋል። በኢትዮጵያ ያሉ ተቃዋሚ ድርጅቶች በሙሉ ከተባበሩ አስተማማኝ የሰላም ትግል አርበኛ ሊፈጥሩ ይችላሉ። ስለሆነም ይኸ ያረጀ እና ያፈጀ መንግስትን የመቆጣጠሪያ ወይንም የመለወጫ ባህል ወደ ቤተ መዘክር መግባት የነበረበት ዛሬ ሳይሆን ትናንት ነበር። ስለዚህ የትጥቅ ትግል ተመራጭ መንገዳችን አይደለም በማለት መደምደም እንችላለን።

**(2ኛ) እጅ አጣምሮ በመቀመጥ የኢህአዴግን በጎ ፈቃደኛነት የመጠበቅ አማራጭ**

*ይህ አማራጭ ምንም ያለማድረግ አማራጭ ነው። በኢትዮጵያ የነጻ ፉክክር ፖለቲካ በኢህአዴግ/ህውሃት ቀውስ ውስጥ እንዲገባ በተደረገበት ሰዓት ምንም ያለማድረግ አማራጭ እጅግ መጥፎ አማራጭ መሆኑ ግልጽ ነው። ስለሆነም ይኼም አማራጭ መንገዳችን አይደለም።*

የአቶ መለስ ምኞት ኢህአዴግ/ህውሃት ፓርቲ በስልጣን ላይ 40 እና 50 አመቶች ያህል እንዲቆይ ማድረግ ስለመሆኑ በተለያዩ አጋጣሚዎች ተናግረዋል። በቅርብ ጊዜ ስልጣን የመልቀቅ ምኞት ያላቸው ሰው አይደሉም። ምክንያቶች ልስጥ።

(1) ከታሪካችን ብንነሳም አንድ ሰው እራሱን የሚያከብርበትን፣ እንደልቡ የወደደውን የሚሾምበትን እና የሚያበለጽግበትን፣ የጠላውን የሚሽርበትን እና የሚያደኽይበትን፣ የተፈታተነውን የሚቀጣበትን የመንግስት ስልጣንን በፈቃደኛነት ለባላንጣው አሳልፎ የሰጠበት ታሪክ የለንም። ይኼን ማድረግ በሰው ልጅ ባህሪም የተለመደ አይደለም። እንደሚታወቀውም ኢህአዴግ/ህውሃት የተባለው ፓርቲ ስልጣን ላይ የወጣው መንግስቱ ኃይለማሪያም በፈቃዱ ለቆለት ወይንም ከደርግ ፓርቲ ጋር  በምርጫ ተወዳድሮ አሸንፎ አይደለም። በኃይል ፈንቅሎ ነው። በዚህ አይነት መንገድ በእጁ ያስገባውን ስልጣን በሰላማዊ መንገድ ህግ አክብሮ የመንግስትን ስልጣን በእጁ ማቆየት ደካማ ጎኑ በመሆኑ በምርጫ 2002 በድምጽ ዘረፋ ተሰማራ። አብዮታዊ ዴሞክራሲ የሚለው መመሪያቸውም ስለ ልማት እየዘመረከ፣ ደሞክራሲን አዳከመህ ስልጣን ላይ ቆይ ስለሚል ነፃ የምርጫው ቦርድ እና ብዙ ነፃ ታዛቢዎች ተሰማርተው ቁጥጥር እስካካልተደረገበት ድረስ ኢህአዴግ/ህውሃት የህዝብ ድምጽ ወደፊትም ከመዝረፍ አይመለስም።

(2) የኢህአዴግ/ህውሃት ባሰልጣናት በሽግግር መንግስታቸው ዘመን የተጻፈውን ህገ መንግስት “ህገ መንግስታችን ነው” ብለው ያውጁ እንጂ የአስተሳሰብ እና የባህል ለውጥ አላደረጉም ነበር። ህገ መንግስቱ ውስጥ የተጠቀሱትን የሙብት ድንጋጌዎች የማያውቋቸው የኢህአዴግ/ህውሃት ባለስልጣኖች ቁጥራቸው ብዙ እንደሚሆን መገመት አያዳግትም። እንደነ መለስ አይነቶቹ ዋናዎቹ ባለስልጣኖች ደግሞ ቢያውቋቸውም ብዙም የሚያምኑባቸው አይመስለኝም። ስለሆነም በፉክክር ቢሸነፉ እንኳን የስልጣን ፍላጎታቸውን መቆጣጠር ችለው ምንም አይነት ጫና በሌለበት ሁኔታ ህገ መንግስቱን አክብረው ስልጣን ይለቃሉ ብሎ መገመት አስቸጋሪ ነው። ጫና ያስፈልጋል። ጥርስ ያለው ጫና ይመረጣል።

(3) አቶ መለስን የውጭ አገር ጋዜጠኞች መቼ ስልጣን እንደሚለቁ ሲጠይቋቸው ከአምስት አመት በኋላ (በምርጫ 2007) በማለት መልስ ሲሰጡ ሰምተናል። ይሁን እንጂ ይኽ የአቶ መለስ መልስ በጥንቃቄ መወሰድ ያለበት ይመስለኛል። የስውር መንግስቱ (ህውሃት) መሪ በመሆናቸው በስውር ኢህአዴግን እየመሩም ከስልጣን ወርጃለሁ ሊሉን ይችላሉ። አዲስ ህግ በማውጣት ወይንም ፓርቲዬ አስገደደኝ በሚል የስልጣናቸውን መጠሪያ ቀየር አድርገው

(4) ለኢህአዴግ/ህወሃት ባለስልጣኖች የመንግስት ስልጣን ማለት የከፍተኛ ደሞዝ እና የድሎት ኑሮ ምንጭ ማለት ነው። እንደ ኢትዮጵያ አይነቷ ደሃ አገር ውስጥ ባላቸው የዕውቀት ደረጃ ከመንግስት ውጭ ባሉ ጥቂት የስራ መስኮች ሌላውን ብሩህ ተፎካካሪ ዜጋ በልጠው የተሻለ ክፍያ እንደማያገኙ ያውቁታል። በምርጫ 2002 ከ90 ከመቶ በላይ ድምጽ አገኘን ማለታቸው እራሱ የኢህአዴግ/ህውሃት ባለስልጣኖች ከስልጣን ላለመውረድ ያልፈነቀሉት ድንጋይ እንዳልነበር ቁልጭ አድርጎ ያሳያል።

(5) ስልጣን ለመልቀቅ ፈቃደኛ የማይሆኑበት ሌላው ምክንያት ደግሞ ደርግን መጣላቸውን እንደውለታ መቁጠራቸው ነው። ስለዚህ የኢትዮጵያ ህዝብ የመገዛት እዳ እንዳለበት አድርገው ያስባሉ። ተቃዋሚዎችም ቢሆኑ ደርግን ለመጣል የኢህአዴግ/ህውሃትን ያህል አስተዋጽኦ ስላላደረጉ ኢህአዴግ/ህውሃት ለተቃዋሚዎች በጎ አድራጊዋ ማዘር ተሬሳ (Mother Teresa) መሆን የለበትም ብለው ያምናሉ። ስለዚህ በስልጣን ላይ ለረጅም ጊዜ መቆየታቸው ተገቢ እና ትክክለኛም ነው ብለው ያምናሉ።

(6) አቶ መለስ ግንቦት 17 ቀን ባደረጉት የድል አድራጊነት ድራማ ላይ ፓርላማውን ሙሉ በሙሉ ኢህአዴግ መቆጣጠሩ የአንድ ፓርቲ ስርዓት አያመጣም ወይ ተብለው ሲጠየቁ የሰጡት መልስ ህገ መንግስቱ ስለማይፈቅድ አይቻልም የሚል ነበር። ይህን ይበሉ እንጂ አቶ መለስ የሚታወቁት ህገ መንግስቱን በማክበር ሳይሆን ህገ መንግስቱን የጠሉትን ማጥቂያ በማድረግ፣ ህገ መንግስቱ አልመች ሲላቸው ደግሞ ከህገ መንግስቱ በላይ በመሆን ሲጥሱት ወይንም ህገ መንግስቱ ላይ ያሉትን መብቶች የሚገድቡ ህጎች በ24 ሰዓቶች ውስጥ አሳውጀው ተፈጻሚ የሚያደርጉ ሰው በመሆናቸው ነው። ስለሆነም የሚናገሩትን አምኖ መቀመጥ ያስቸግራል። በምርጫ 2002 የህዝብ ድምጽ በመዝረፍ የመደብለ ፓርቲ ስርዓት ቀውስ ውስጥ እንዲገባ ማድረጋቸውም ግልጽ ነው።

(7) በዚሁ ግንቦት 17 ቀን በመስቀል አደባባይ ባደረጉት ድራማ ላይ ፓርቲያቸው እንደ ጃፓን ሊብራል ዲሞክራቲክ ፓርቲ ወይንም እንደ ስዊድን ሶሻል ዲሞክራቲክ ፓርቲ ረዘም ላለ ጊዜ ስልጣን ላይ ሊቆይ እንደሚችል በንግግራቸው ጠቁመዋል። አንባቢ ልብ በል። የስዊድን ሶሻል ዴሞክራቲክ ፓርቲ እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር ከ1940 እስከ 1988 ዓመተ ምህረት ድረስ ለ48 አመቶች ያህል ጊዜ ስልጣን ላይ በመቆየት በአለም የፓርቲዎች ታሪክ ስኬታማ

(ሀ) የስዊድኑ ፓርቲ 40 ከመቶ እስከ 50 ከመቶ በሆነ እንዲሁም የጃፓኑ ፓርቲ 42 ከመቶ እስከ 58 በመቶ የህዝብ ድምጽ ድጋፍ እንጂ እንደሳቸው ፓርቲ በ90 ከመቶ በላይ የህዝብ ድምጽ ሁለቱም ፓርቲዎች በታሪካቸው አግኝተው አያውቁም። ይኽ በራሱ በ2002 ምርጫ በኢትዮጵያ ነፃ ፉክክር አለመደረጉን ይናገራል።

(ለ) እነዚህ ሁለት ፓርቲዎች በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ የፓርቲ አባል እንጂ እንደ ኢህአዴግ/ህውሃት አምስት ሚሊዮን የፓርቲ አባል እና አንድ የፓርቲ አባል ሌላ አምስት ዜጎችን እንዲይዝ የሚያደርግ የማፊያ ካድሬዎች መዋቅር እንዳልነበራቸው አልነገሩንም።

(ሐ) እነዚህ ሁለት ፓርቲዎች እንደ ኢህአዴግ/ህውሃት ህገ መንግስታዊ መብቶችን አፍራሽ እና ገዳቢ ሳይሆኑ ህገ መንግስት አክባሪዎች እና አስከባሪዎች እንደነበሩ ደብቀውናል።

(መ) እነዚህ ሁለት ፓርቲዎች ኢህአዴግ/ህውሃት እንደሚያደርገው የተቃዋሚ እጩዎችን እና የታቃዋሚ ታዛቢዎችን የማያሳድዱ፣ የማይደበድቡ፣ የማያስሩ፣ የማይገድሉ፣ በፉክክር የሚያምኑ እና በህዝብ ድጋፍ እንጂ በጠበንጃ ለመግዛት የማይሞክሩ ሰላማዊ፣ ስልጡን እና ዴሞክራሲያዊ ፓርቲዎች እንደነበሩ አቶ መለስ አልገለጹም።

(ሠ) ህዝቡ ፈርቶ ኢህአዴግን/ህውሃት እንዲመርጥ የስራ ለምግብ (ሴፍቲ ኔት) ፕሮግራምን በምርጫ 2002 ህዝብ ማስፈራሪያ እና መደለያ እንዳደረገው እነዚህ ፓርቲዎች በአገራቸው ለህዝብ የሚደረጉ ድጎማዎችን ለፖለቲካ መጠቀሚያ ማስፈራሪያ እንደማያደርጉ አቶ መለስ ደብቀውናል።

(ረ) በኢትዮጵያ የኢህአዴግ መንግስት የኢህአዴግ/ህውሃት ፓርቲ መዋቅር ነው። ልዩነት የለም። እነዚህ ፓርቲዎች በሚመሩት መንግስት እና በፓርቲያቸው መካከል ግን ግልጽ የሆነ መራራቅ እንደሚኖር እና የመንግስትን ሃብት ለፓርቲያቸው ጠቀሜታ ከማዋል የተቆጠቡ ህግ አክባሪ ፓርቲዎች እንደነበሩ አቶ መለስ ደብቀውናል።

(ሰ) በመጨረሻ የስዊድን ምርጫ አስተዳደር እና የጃፓን የምርጫ አስተዳደር ኮምሽን እንደ የኢትዮጵያ የምርጫ ቦርድ የኢህአዴግ/ህውሃት ፍጡሩ እና የህዝብ ድምጽ ዘራፊ ሳይሆኑ በስልጣን ላይ ካለው ገዢ ፓርቲ ነጻ የሆኑ እና አመሰራረታቸውም ነጻነታቸው እንዲጠበቅ ተድርጎ ስለመሆኑ አቶ መለስ አልነገሩንም።

ሲደመደም፣ አቶ መለስ እና ፓርቲያቸው ከምርጫ 2002 ወዲህ ተጨማሪ ሌላ ለ10 እና ለ20 አመታት ወይንም ከዚያ በላይ ለሆነ ጊዜ ስልጣን ለመቆየት ምኞት ስላላቸው ካለምንም ጫና እና ከባድ ፉክክር በፈቃዳቸው ዴሞክራሲ በኢትዮጵያ እንዲያብብ ብለው የተከፋፈሉ ደካማ ተቃዋሚ ፓርቲዎች በሞሉባት ኢትዮጵያ  በቀላሉ ተሸንፈው ስልጣን ይለቃሉ በሚል ተስፋ እጅ አጣምሮ መቀመጥ ላም ባልዋለበት ኩበት ለቀማ ስለሚሆን ይኽ አማራጭ ውድቅ ነው።

**(3ኛ) ሰላማዊ እና ህጋዊ ትግል አማራጭ**

የሰላም ትግል እንደ ትጥቅ ትግል ፖለቲካውን በጠመንጃ ሳይሆን በነፃ ፉክክር ያራምዳል። በድምጽ ማጉያ ያራምዳል። ድምጽ ማጉያ ሰው አይገድልም። በድምጽ ማጉያ የህክምና ጣቢያዎች፣ ትምህርት ቤቶች፣ ፋብሪካዎች፣ የፖሊስ ጣቢያዎች፣ የጦር መንደሮች ወ.ዘ.ተ. አይፈርሱም። ስልጣን ላይ የሚወጡትም ህዝቡ አውቆ የመረጣቸው ስለሚሆኑ ስልጣን ላይ ከመውጣታቸው በፊት ያውቃቸዋል። ይኼ መንገድ ህዝቡን የስልጣን ባለቤት ያደርጋል። የህዝብ ተሳትፎ ከፍ ያለ ነው። የመንግስት ሽግግር የሚደረገው ህዝቡ በየአካባቢው የፈለገውን በሰላማዊ መንገድ በመምረጥ ስለሚሆን የህዝብ ድምጽ እስከተከበረ ድረስ በዚህ አይነት መንገድ የሚመሰረተው መንግስት በሁሉም የአገሪቱ ክፍል ተቀባይነት ይኖረዋል። በህዝቡ መካከል ክፍፍል አይኖርም። ሰላማዊ ትግል ስብዕናውም ከፍ ያለ ነው። ለዲሞክራሲ ግንባታም አጋዥ ነው። እንደ ኢትዮጵያ አይነቷ አገር ውስጥ በጠመንጃ ስልጣን ላይ የተቀመጠ ፓርቲ እስካለ ድረስ ከፍ ብለን በ(1ኛ) እና በ(2ኛ) አማራጮች ስር በዘረዘርናቸው ምክንያቶች ላይ ኋላቀርነታችን ተጨምሮበት የሰላም ትግል ቀላል እንደማይሆን መገመት አለብን። ቢሆንም ግን ከትጥቅ ትግል አማራጭ እና ከእጅን አጣምሮ መቀመጥ አማራጭ የሰላም ትግል አማራጭ የተሻለ በመሆኑ ህዝብን ለስልጣን ባለቤትነት ያበቃል። አገርን ለመፍርስ አያጋልጥም። ስለዚህ ተመራጩ መንገዳችን የሰላም ትግል ነው።

እርግጥ በምርጫ የህዝብ ይሁንታን ማግኘት የገዢነት መብት እና ስልጣን ምንጭ ነው። ይኼ ትልቁ የፖለቲካ ኃይል ምንጭ ነው። ነገር ግን 90 ከመቶ በላይ የህዝብ ይሁንታን አገኘሁ የሚል ፓርቲ አንድም የሚያወራውን አያውቅም አሊያም ዘርፎ ነው። በተለይም እንደ ኢትዮጵያ ባለች

ህብረ ብሔራዊ አገር፣ የፖለቲካ እና የኢኮኖሚ ምኞቶች እጅግ በተራራቁበት፣ አብዛኛው ህዝብ በችግር ላይ በሚገኝበት፣ ገዢው ፓርቲ በአገር ሉዓላዊነት ጉዳይ በማይታመንበት አገር ውስጥ ህዝቡ ለ18 አመቶች ስልጣን ላይ የነበረውን ፓርቲ 90 ከመቶ በላይ የድጋፍ ድምጽ ሰጠው ቢባል አዕምሮውን በሚጠቀም ሰው ዘንድ ተቀባይነት የለውም። የኢህአዴግ/ህውሃት መሪዎች ቂሎች ስላልሆኑ ዘርፈው መሆን አለበት 90 ከመቶ ያገኙት። ዘርፈው ከሆነ ደግሞ መዝረፍ ያስቻሉዋቸው ሌሎች የፖለቲካ ኃይሎች አሉዋቸው ማለት ነው። እነዚህ የፖለቲካ ኃይሎች (ትብብሮች) የሚመነጩት ከሰማይ ሳይሆን ከህብረተሰቡ ውስጥ ነው። ከእነዚህ ምንጮች የሚፈስለትን እየተመገበ ነው በ90 ከመቶ በላይ ድምጽ አሸነፍኩ ለማለት የበቃው። ተቃዋሚው እነዚህን የኢህአዴግ/ህውሃት የፖለቲካ ኃይል ምንጮች መቆጣጠር ሲችል ብቻ ነው ቁም ነገር ሊያመጣ የሚችለው። ይኼ የሚደረገው በሰላማዊ ትግል ስለሆነ ከገዢው ፓርቲ ጋር መኮራረፍም አያስፈልግም። ዋና ዋናዎቹን ምንጮች እንመልከት።

(1) የተቃዋሚ ፓርቲዎች ክፍፍል

አንዱ ትልቁ የኢህአዴግ/ህውሃት የፖለቲካ ኃይል ምንጭ የተቃዋሚው መከፋፈል ነው። ድንገት ተከስቶላቸው ይሁን ወይንም በደረሰባቸው ውድቀት አፍረው ባይታወቅም የአንዳንድ ተቃዋሚ ፓርቲ መሪዎች ምርጫ 2002 ተከትሎ ስለምርጫው መግለጫ ሲሰጡ በመከፋፈላቸው ኢህአዴግን ተጠቃሚ ሊሆን መቻሉን ጨምረው ሲናገሩ ነበር። የኢትዮጵያ ህዝብ ግን ተባበሩ አለተበለዚያ ተሰባበሩ ሲላቸው ከ5 አመቶች በላይ አልፈውታል። ህጋዊ እና ሰላማዊ ትግል ተቃዋሚ ፓርቲዎች ለህልውናቸው ሲሉ በአስኳይ መተባበራቸው አለባቸው። መኢአድ የመድረክ አባል ድርጅት ሆኖ የሚሰራበትን ሁኔታን በመፍጥር ህብረት መገንባት ቢጀመር ጥሩ ይመስለኛል። በኢትዮጵያ ውስጥም ውጭም የምንገኝ ዜጎች ግፊት ማድረግ የምችል ይመስለኛል።

(2) በህገ መንግስቱ ውስጥ ያሉ ጉድለቶች እና ህገ መንግስታዊ መብቶችን መጣስ ወይንም መገደብ

ኢህአዴግ/ህውሃት እነዚህን በመጠቀም የመጫወቻውን ሜዳ ለኢህአዴግ እንዲያደላ ያደርጋል። ስለሆነም ይኸ ለኢህአዴግ/ህውሃት የፖለቲካ ኃይል ምንጭ ነው። ይኸ ምንጭ ቁጥጥር ሊደረግበት ይገባል። በህገ መንግስቱ ጉድለት ባለባቸው ድንጋጌዎች፣ በተጣሱ እና በተገደቡ ህገ መንግስታዊ መብቶች ላይ ምሁራን ውይይት ቢከፍቱ ጠቃሚ ይመስለኛል። ኢህአዴግ ህዝቡ እንዳያቃቸው የሚፈልጋቸው ህገ መንግስታዊ መብቶቹን ጨምሮ በዝርዝር እንዲያውቅ ቢደረግ በተወሰነ ደረጃ ከፍራቻ ነፃ ሊወጣ የሚችል ይመስለኛል። ህዝብ እንዲያውቅ በማድረግ ረገድ ነፃ ፕሬስ ከፍተኛ ሚና ሊጫወት ይችላል።

(3) የምርጫ ቦርድ እና የምርጫ አስፈጻሚዎች

ይኸ ተቋም እና በውስጡ የተሰማሩት ሰራተኞች የኢህአዴግ/ህውሃት ፍጡር እና ደሞዝተኞች በመሆናቸው የኢህአዴግ/ህውሃት ፓርቲ ታማኝ አገልጋዮች ናቸው። ፓርቲ ፉክክሩ በሚዛናዊ ሜዳ እንዳይደረግ እና በገለልተኛ ዳኛ እንዳይዳኝ በማድረግ የኢህአዴግ/ህውሃት ፓርቲ እርሱን ሲጠቅም ተቃዋሚውን ጎዳ። መጪ ምርጫዎች ፋይዳ እንዲኖራቸው በቅድሚያ በዚህ የኢህአዴግ/ህውሃት የፖለቲካ ኃይል ምንጭ ላይ ቁጥጥር ሊደረግ ይገባ።

(4) የመንግስት ተቋሞች

በኢህአዴግ/ህውሃት ፓርቲ እና በኢህአዴግ/ህውሃት መንግስት መካከል ልዩነት የለም። የመንግስት ተቋሞች ከፓርቲ ነጻ መሆን ሲገባቸው ከፌደራል እስከ ቀበሌ ድረስ ያሉት የመንግስት መስሪያ ቤቶች የኢህአዴግ/ህውሃት ፓርቲ መዋቅሮች በመደረጋቸው ትብብር ለኢህአዴግ/ህውሃት ፓርቲ ለጋሽ እና ለተቃዋሚ ፓርቲዎች ነፋጊ ሆነዋል። ተቃዋሚ ፓርቲዎች ፈቃድ ቢጠይቁ ይጓተትባቸዋል ወይንም አይቻልም ይባላሉ። በምርጫ ጊዜም ቀበሌዎች የኢህአዴግ/ህውሃት ፓርቲ ቀስቃሽ እና ስራ አፋጥኝ ሲሆኑ በተቃዋሚው እና በተቃዋሚ ደጋፊዎች ላይ ግን የስለላ ድርጅት አስከመሆን ድረስ ግልጋሎት ይሰጣሉ። በዚህ አይነት ኢህአዴግ/ህውሃት ፓርቲ የጨዋታ ሜዳው ለእራሱ እንዲያደላ አድርጓል። ይኸ የኢህአዴግ/ህውሃት ተጨማሪ የፖለቲካ ኃይል ምንጭ ቁጥጥር ሊደረገበት ይገባል።

(5) የውጭ እርዳታ/የዲፕሎማሲ ትግል

ከአሜሪካ እና ከምዕራብ አውሮፓ ለኢትዮጵያ የሚፈሰውን የድጎማ ገንዘብ ገዢው ኢህአዴግ/ህውሃት ፓርቲ ለተቃዋሚ ፓርቲዎች መጨቆኛ አድርጎታል። ስለዚህም 90 ከመቶ በላይ ድምጽ ለማግኘት ተጨማሪ የፖለቲካ ኃይል ምንጭ ሆኖለታል። በምርጫ 2002 እንደታዘብነው ገዢው ፓርቲ ይኸን እርዳታ በመጠቀም በኢትዮጵያ የመድብለ ፓርቲ ስርዓት እንዲተኛ እና የአንድ ፓርቲ ስርዓት ከተኛበት እንዲነሳ አድርጓል። በሌላ በኩል ከውጭ ገንዘብ ማሰባሰብን ህገ ወጥ በማድረግ ተቃዋሚ ፓርቲዎች የገንዘብ ምንጫቸው ደካማ እንዲሆን አድርጓል። በዚህ አይነት በኢትዮጵያ የፉክክር ሜዳው ፍጹም ለኢህአዴግ/ህውሃት ያደላ እንዲሆን ተደርጓል። ስለሆነም የውጭ እርዳታ ወደ ኢትዮጵያ የሚፈሰው በኢትዮጵያ የአንድ ፓርቲ ስርዓትን ሊያጠጣና ሊያለመልም ከሆነ መቆም አለበት። በዚህ ረገድ ውጭ ያለው ኢትዮጵያዊ የዲፕሎማሲ ትግሉን ከፍ ማድረግ ያለበት ይመስለኛ። የአሜሪካ መንግስት እና የአውሮፓ ህብረት የአንድ ፓርቲ ኮምኒስት ስርዓት በኢትዮጵያ በመመስረታቸው እንዲያፍሩ መደረግ አለበት።

የዲፕሎማሲ ትግሉን ጋል በማድረግ ይህ ከውጭ ለኢህአዴግ/ህውሃት የሚፈስ የፖለቲካ ኃይል ምንጭ መድረቅ አለበት።

(6) የብዙሃን ዜና ድርጅት

ኢህአዴግ/ህውሃት የአገር የሆነውን የኢትዮጵያ የብዙሃን ዜና ማሰራጫዎች በግሉ በመያዝ እንደልቡ መጠቀም ሲችል ተቃዋሚ ፓርቲዎች አይችሉም። በሌላ በኩል የግል ቴሌቪዥን እንዲኖር አልተደረገም። ከኢህአዴግ/ህውሃት ጋር ተባባሪ ለማይሆኑ ግለሰቦች የሬዲዮ ፈቃድ ይከለከላል። ነፃ የህትምት ጋዜጣዎችን እንዲዳከሙ ይደረጋል። ቪኦኤ አማርኝ ስርጭትን እና የጀርመን ሬዲዮ አማርኛ ፕሮግራም ታፍነዋል። በርካታ ድህረ ገጾች ተጋርደዋል። እነዚህን ሁሉ በማድረግ ኢህአዴግ/ህውሃት በአንድ ወገን በእጁ በያዛቸው ዜና ማሰራጫዎች ጠዋት ማታ እራሱን ከመራጩ ህዝብ ጋር ሲያስተሳስር በሌላ ወገን መራጩ ህዝብ ነጻ መረጃዎችን እንዳያገኝ እና ከተቃዋሚ ፓርቲዎች እንዲራራቅ አድርጓል። ይኽን በማድረግ ኢህአዴግ/ህውሃት የሚዲያ ሜዳ እራሱን እንዲጠቅም ተቃዋሚውን እንዲጎዳ በማድረግ የፉክክሩን ሜዳ ወደሱ እንዲያደላ አድርጓል። ይኽ ለኢህአዴግ/ህውሃት ከፍተኛ የፖለቲካ ኃይል ምንጭ ሆኖ ሲያገለግለው ቆይቷል። ተቃዋሚ ፓርቲዎችም ህዝባቸውን የመድረስ መብታቸው መከበር አለበት። መላ መፈለግ አለበት።

(7) ባለሙያዎች

የቪኦኤን አማርኛ ፕሮግራም ስርጭት በኢትዮጵያ ለማፈን ኢህአዴግ/ህውሃት ጦር ማንቀሳቀስ አያስፈልገውም። የተቃዋሚ ድርጅቶችን ስልክ ለመጥለፍ እና ሌሎች ተጨማሪ ተግባራትም ለመፈጸም የባለሙያዎች ትብብር በቂ ነው። ስለሆነም የባለሙያዎች ትብብርም ለኢህአዴግ/ህውሃት ተጨማሪ የፖለቲካ ኃይል ምንጭ ነው። ይኼን ኃይል በመጠቀም የፉክክሩን ሜዳ ወደ እሱ እንዲያደላ አድርጓል። ስለዚህ ባለሙያዎች በዚህ ረገድ ለኢህአዴግ የሚለግሱት ትብብር የአንድ ፓርቲ ስርዓት በኢትዮጵያ መልሶ እንዲበቅል ማድረጉን፣ በተግባራቸው አገራቸውን እና ህዝባቸውን እየጎዱ መሆኑን በውይይት እንዲገነዘቡት በማድረግ በዚህ የኢህአዴግ/ህውሃት የፖለቲካ ኃይል ምንጭ ላይ ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል።

(8) የአገር ሃብት ምንጮች ቁጥጥር እና የሰራተኞች ትብብር

አንድ ገዢ ቡድን በንብረት፣ በተፈጥሮ ሃብት፣ በፋይናንስ ሃብት፣ በኢኮኖሚ ዘርፍ፣ በመገናኛና በትራንስፖርት ላይ ያሉት ቁጥጥሮች በሙሉ በአገር ሃብት ምንጮች ላይ ያሉት ቁጥጥሮች ናቸው። እነዚህ የሃብት ምንጮች ለገዢው ቡድን ገቢያውንና የውጭ ምንዛሬን ለመቆጣጠርና ቀውስን ለማርገብ፣ ለመከላከያ፣ ጸጥታና ቢሮክራሲው ደሞዝ ለመክፈል፣ መሳሪያ ለመግዛትና

የመሳሰሉትን ለማድረግ ይረዱታል። ስለዚህ በእነዚህ የተለያዩ የሃብት ምንጭ ዘርፎች የሚገኝ የህዝብ ትብብር ከፍተኛ ከሆነ ገዢው ቡድን ከዚህ ምንጭ የሚያገኘው የፖለቲካ ኃይል ከፍተኛ ሲሆን ትብብሩ ዝቅተኛ ከሆነ ደግሞ የሚያገኘው የፖለቲካ ኃይል ዝቅተኛ ይሆናል። ይህ የፖለቲካ ኃይል ምንጭ ከባንክ፣ ከተለያዩ ፋብሪካዎች እና ኩባንያዎች፣ ከኢንቨስትሜንት ድርጅቶች፣ ከትራንስፖርት፣ ከንግድ ድርጅቶች፣ ከኢነርጂ አመንጪ ድርጅቶች፣ ከንዱስትሪ ድርጅቶች እና በእነዚህ ድርጅቶች ውስጥ ከሚሰሩ ሰራተኞች የሚገኝ ትብብርን ያካትታል። ስለዚህ በዚህ የፖለቲካ ኃይል ምንጭ ላይ ቁጥጥር ማድረግ ወይንም እንዲደርቅ ማድረግ አስፈላጊ ሊሆን ይችላል። ስራ ማቆም ሰላማዊ ትግል ነው። መብትም ነው። ዛሬ ኢትዮጵያ አጠቃላይ አገር አቀፍ ስራ ማቆም ለማድረግ ዝግጁ ላትሆን ትችላለች። ወደፊት ግን ትሆናለች።

(9) የጸጥታ እና የመከላከያ ኃይሎች ትብብር

በህገ መንግስቱም እንደተገለጸው ይህ ኃይል ከፖለቲካ ገለለተኛ በመሆን ታዛዥነቱ ለህገ መንግስቱ ብቻ መሆን ሲገባው ህገ መንግስቱን በመጣስ ከፍተኛ ሹማምንቶቹን የፓርቲ አባል በማድረግ ይኸ ተቋም የኢህአዴግ/ህውሃት የፖለቲካ ኃይል ምንጭ ተደርጓል። የኢትዮጵያን ህዝብ በፍራቻ ለመግዛት መጠቀሚያ ሆኗል። ስለዚህ የኢትዮጵያን መለዮ ለባሽ ማስተማር ያስፈልጋል።

ሲደመደም፥ በራስ እምነት ካለ፣ አርቆ አስተዋይነት ካለ፣ ትዕግስት ካለ፣ ጽናት ካለ ማድረግ የማይቻል ነገር የለም። ስኬታማ ሰላማዊ ትግል ለማድረግ የሰላም ትግል መሪዎች ትክክለኛ ግብ (ዓላማ) መንደፍ ይኖርባቸዋል። ግብ (ዓላማ) መድረሻ ወይንም ምኞት ነው። ከዚያ ለእያንዳንዱ ግብ (ዓላማ) ስትራተጂ መቀየስ አለባቸው። ስትራተጂ ደግሞ ግብ (ዓላማ) ወይንም ምኞት ማስፈጸሚያ ነው። ከዚያ ለእያንዳንዱ ስትራተጂ አንድ ወይንም ከዚያ በላይ ስልቶች መንደፍ አለባቸው። ስልት ወይንም ስልቶች ስትራተጂ ማስፈጸሚያ ተግባሮች ናቸው። ስልቶች ከሁኔታ ሁኔታ ሊለዋወጡ ይችላሉ። ለምሳሌ አንድን ተመሳሳይ ስትራተጂ ለማስፈጸም አምባ ገነን ገዢዎች ጨካኝ እርምጃ መውሰድ በጀመሩበት እና ባልጀመሩበት ሰዓት የሚቀየሱ እና ስራ ላይ የሚውሉ ስልቶች ሊለያዩ ይችላሉ። ስትራተጂ እንደ ስልት አይቀያየርም። ስትራተጂ ሲቀየስ ትልቅ ጥንቃቄ መደረግ አለበት። በስትራተጂ ላይ የሚፈጸም ስህተት እጅግ አደገኛ ነው። የተሳሳተ ስትራተጂን ከተከተልን ወደ ፈለግንበት መድረሻ (ግብ) አንደርስም። እነዚህን ከፍ ብለን የዘረዘርናቸውን የኢህአዴግ/ህውሃት የፖለቲካ ኃይል ምንጮች እና የሰላም ትግል አኪያሄዶች ወደፊት የምንመለስባቸው፣ በስፋት እና በጥልቀት የምንወያይባቸው ጉዳዮች ናቸው። እስከዚያው መልካሙን እመኛለሁ። . . . አመሰግናለሁ . . . ግርማ ሞገስ።